## ሙስናን በጋራ ለመታገል የባለድርሻ አካላት ሚና

### የመንግስት ሚና

የመግስት ስርዓትን እየተፈታተነ እና ጠንካራ የሀገረ መንግስት ግንባታ እንዳይሰለጥ ማነቆ የሆነውን ሙስና ለመታገል የሚያስችል አስቻይ ሁኔታ መፍጠር ይጠበቃል። ግልፅነትን፣ ተጠያቂነትን እና ማህበራዊ የሞራል ልዕልናን የሚያጠናክሩ ህጎችን፣ ፖሊሲ፣ ደንብ እና መመሪያዎችን በመቅረፅ፣ ዓለማቀፍ ትብብርን በማጠናከር፣ ትግሉን የሚያስቀጥል ተቋማዊ አቅምና ተቋሙን የሚመራ ሰብዓዊ አደረጃጀት መፍጠር፣ ተቋማቱ በጋራና በቅንጅት መስራት የሚችሉበት መድረክ መፍጠር፤ የተጠያቂነት ስርዓትን መዘርጋትና አጥፊዎች ላይ የማያዳግም እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ከመንግስት ይጠበቃል።

### የቤተሰብ ሚና

ቤተሰብ የመጀመሪያው የልጆች የስነምግባር ትምህርት ቤት ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው የሚመክሯቸውን ምክር በተግባር በመኖር ሊያሳዩዋቸው ይገባል። ወላጆች በልጆቻቸው ስነ ምግባር ላይ ከትምህርት ቤት ጋር በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና የተማሪና የትምህርት ቤት ንብረት መስረቅ፣ አስተማሪ አለማክበርን፣ ኩረጃን የመሳሰሉ መጥፎ ተግባራትን እንዲጠየፉ ቀጣይነት ባለው በቤተሰባዊ ንግግር ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪም ወላጆች ከሃይማኖት ተቋማት ጋርም መልካም እሴት በሚገነባበት ሁኔታዎች መመካከር፤ ልጆች የተማሩትን ትምህርት ተግባራዊ እንዲያደርጉ በመምከር ስነምግባራቸውን መቅረፅ ያስፈልጋል።

### የሲቪክ ማህበራት ሚና

ከፖሊቲካ እንቅስቃሴ ነፃ የሆኑ ተቋማት በመሆናቸው የመንግስትን አሰራር፣ ግልፅነት፣ አደረጃጃትና ተጠያቂነት ከህዝብ ተጠቃሚነት አንፃር መፈተሽ ያስፈልጋል። ሁሉን አቀፍ ፍትህ እንዲሰፍን፣ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት እዲረጋገጥ፣ የሙስና መከላከልና የስነምግባር ግንባታ ስራዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በመስራት በመንግስትና በህዝብ መካከል መተማመን እንዲፈጠር ለማስቻል ከሚመለከታቸው አጋርና ባለደርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መስራት ያስፈልጋል።

### የሚዲያ ሚና

ሚዲያ የሙስናን ምንነት፤ መንስኤውን፣ ጉዳቱንና የመከላከያ ሥልቶቹን በማስተማር ኅብረተሰብ የፀረ-ሙስና ትግሉ አጋር እንዲሆን ማድረግ አለበት። የሙስና ወንጀሎችን በማጋለጥ፣ የሙስናን አክሳሪ ባሕርያት ማሳየት እና በምርመራ ጋዜጠኝነት አማካኝነት ከተለያዩ ወገኖች አቤቱታዎችን፣ ጥቆማዎችን፣ ፍንጮችን፣ መሠረት በማድረግ እየመረመረና እየተከታተለ የተደበቁ እውነታዎችንና ድርጊቶችን ፈልፍሎ በማውጣት በማስረጃና በመረጃ እያስደገፈ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

### የትምህርት ተቋማት ሚና

የዜጎችን ዝንባሌ ግብረ ገብና ባሕርይ የመቅረፅ ስራ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በማከናወን የልጆች አስተሳሰብና ስነምግባርን ለመቅረጽ በሚያወጧቸው ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ዙሪያ በካሪኩለም ዝግጅትና የማሻሻል ስራ ሰርቶ መተግበር ያስፈልጋል። ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በትውልድ ስነምግባር ግንባታ ዙርያ ማጠናከር እንዲሁም ተማሪዎች ከመደበኛ ትምህርት ባሻገር፣ በልዩ ልዩ ክበባት እንዲሳተፉ በማድረግ፣ አዎንታዊ ባሕርይ እንዲገነቡ ማድረግ ያስፈልጋል።

### የእምነት ተቋማት ሚና

ሃይማኖታዊ እሴቶችንና ሕጎችን ማስተማር፣ ምዕመኖቻቸው የፈጣሪያቸውን ትዕዛዝ እንዲያከብሩ ማስተማርና መምከር የእምነት ተቋማት ተከታዮቻቸውን በየሙያ መስኩ እያሰባሰቡና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር እየተቀናጁ የሙያ ስነምግባርን በተመለከተ አማኞች ለሙያቸው ታማኝ እንዲሆኑ ከእምነታቸው አኳያ ማስተማር አለባቸው። የእምነት ተቋማት እርስ በርሳቸውም ተሞክሯቸውን እንዲለዋወጡ ማድረግ እንዲሁም ከሙስና የጸዳ አገልግሎት እንዲሰጡ የጋራ ጥረት ማድረግ ይችላሉ።

---


**በስነ ምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ**

አድራሻ
በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ

ጥቆማ ለመስጠት
የነፃ ስልክ መስመር
8887
እንዲሁም በመስመር ስልክ
011 126 61 87
011 126 61 72

Addis Ababa Ethics and Anti-Corruption -ፀረ ሙስና

Addis Ababa Ethics Media

aanticoruption@gmail.co


# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን

**ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን አከባበር አስመልክቶ የተዘጋጀ**

**"ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው፤ በሕብረት እንታገል!"**

ህዳር 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን አከባበር አስመልክቶ የተዘጋጀ

### መግቢያ

ሙስና የሀገርን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ በማናጋት ሀገርን እስከመበተን የሚያደርስ ድንበር ዘለል ወንጀል ነው። ሙስና ዜጎችን ለሥቃይ፣ ለእንግልት እና ለከፋ ድህነት የሚዳርግ አደገኛ ነቀርሳ በመሆኑ በጋራ መታገል ይገባል።

የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የሙስናን አስከፊነት በመረዳት በህብረት ለመዋጋት 140 የሚሆኑ የዓለም ሀገራት የተባበሩት መንግስታት ዓለም ዓቀፍ የፀረሙስና የቃል ኪዳን ስምምነት ሰነድን እ.ኤ.አ ዲሴምበር 9/2003 በሜሪዳ (ሜክሲኮ) ፈርመውታል። የጋራ ስምምነት የፈጸሙበት የቃል-ኪዳን ሰነድ ሥራ ላይ የዋለበትን ዕለት ለማስታወስ በስምምነት ሰነዱ ላይ ዓላማ ብለው የተጠቀሱትን ሙስናን የመከላከል እና የመግታት ጥረት በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማ እና ብቃት ያለው እንዲሆን የማድረግ፣ የተዘረፈ ሀብት እንዲመለስ በማድረግ ወንጀሉን የመከላከል፣ በአባል ሀገሮች የሙስና ትግሉን ለማስፋፋት እና ለማፋጠን እንዲቻል ዓለም አቀፍ ትብብር እና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ ናቸው። ሁሉንም የፀረ-ሙስና ትግል ባለድርሻዎችን ለማነቃቃት የዘንድሮ ዓለም አቀፉ የፀረ-ሙስና ቀን በአለም ለ20ኛ ጊዜ "Uniting the World against Corruption" በሚል መሪ ቃል የሚከበር ይሆናል።

ሀገራችን ኢትዮጵያም እ.ኤ.አ ህዳር 26/2007 ስምምነቱን ማፅደቅዋን ተከትሎ በየዓመቱ በልዩ ልዩ መሪ ቃል በተለያዩ መርሃ ግብሮች በዓሉን ስታከብር ቆይታለች። ለ19ኛ ግዜ በዓሉ "ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው፤ በሕብረት እንታገል!" በሚል መሪ ቃል ከህዳር 1 እስከ 27/2016 ይከበራል።

ይህ መሪ ቃል ለበዓሉ የተመረጠበት ምክንያት ሙስና ያለ ልዩነት ሁሉንም ኢትዮጵያውያንና የከተማችንን ነዋሪ የሚጎዳ፣ ውስብስብ፣ ድንበር ተሻጋሪ እና ዓለም አቀፍ ችግር መሆኑን በመገንዘብ የጋራ ጠላት የሆነውን ሙስና በጋራ መታገል በማስፈለጉ ይህ የግንዛቤ ማስጨበጫ ብሮሸር ተዘጋጅቷል

### የበዓሉ አከባበር ዓላማ

◊ በጸረ ሙስና ትግሉ እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን አጠናክሮ ለማስቀጠልና የቀጣይ ትኩረት መስኮች ለማመላከት፤
◊ በከተማ ደረጃ የተጀመረውን የትውልድ ስነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ጥረት ለማጠናከር፤
◊ በጸረ ሙስና ትግሉ ሚና ያላቸውን ባለድርሻ አካላትና ህብረተሰቡን በስፋት በጸረ ሙስና ትግሉ ለማስገባት፤
◊ የጸረ-ሙስና ትግሉን ህዝባዊ መሰረት በማስያዝ የዜጎችን የጋራ ተጠቃሚነት ለረጋገጥ ግንዛቤ መፍጠር፤
◊ የጸረ ሙስና ትግልን በማጠናከር የአገልግሎት አሰጣጥና መልካም አስተዳደር ለማስፈን የግንዛቤ ስራዎችን ለማስፋፋት፤

### የሙስና ጽንሰ ሀሳብ

◊ ሙስና የሀገርን ኢኮኖሚ የሚያዳክም የዜጎችን የጋራ ተጠቃሚነት የሚያሳጣ ድንበር ዘለል ወንጀል ነው።
◊ ሙስና የተሰጠን ሃላፊነትን ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም ማዋል ነው።
◊ ሙስና አደራን መብላት ነው።
◊ ሙስና ለዜጎችን የተሰጠ የመጠቀም መብትን መንጠቅ ነው።
◊ ለግል ወይም ለሌላ ጥቅም ሲባል ስርዓትን፣ ህግን፣ ደንብን እና የአሰራር መርሆችን የመጣስ ተግባር ነው።
◊ በአቋራጭ የመበልጸግ ኢ-ስነምግባራዊ አካሄድ ነው።

### የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

◊ የአፈፃፀሙ ሂደትና ስልት ውስብስብ መሆን፤
◊ በአብዛኛው የባለቤትነት ስሜት መጓደል፤
◊ የፈፃሚዎቹ ማንነት በግልጽ አለመታወቅ ፣
◊ በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደ ነውር አለመታየቱ፤




### ሙስና መንስኤዎች

◊ የሥነ-ምግባር ውድቀት ዋነኛ የሙስና መከሰት ምክንያት ነው፤
◊ የቢሮክራሲዎች መብዛትና ጠንካራ አስተዳደራዊ ስርዓት አለመኖር፤
◊ የዜጎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ማነስ፣ የግልጸኝነትና ተጠያቂነት መጓደል፤
◊ የፕሬስ ነጻነት አለመኖር፤
◊ ገደብ የለሽ ስልጣን መኖር፤
◊ የፖለቲካ አለመረጋጋት፤
◊ የጥቅም ግጭት በአሰራሮች ውስጥ መኖር፤
◊ ያልተማከለ የአሰራር ስርዓት አለመኖር፤

### ሙስና በጋራ የመታገል አስፈላጊነት

የሙስና አፈጻጸሙ እየረቀቀ፣ እየሰፋና በመልካም አስተዳደርና በእድገት ላይ የሚያደርሰዉ ጉደት እየከፋ በመምጣቱ ሙስናን መዋጋትና መከላከል የመልካም አስተዳደርና የልማት ማዕከላዊ አጀንዳ ሆኗል። የዓለም የጸረሙስና ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት ፈርጀ ብዙ የለውጥ እርምጃዎችን በተቀናጀ መልኩ መውሰድ እንደሚጠይቅ ያሳያሉ።

ከነዚህ መካከል የፖሊቲካ አመራሩ ቁርጠኝነት መኖር መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን ጠንካራ የጸረሙስና ህግና አስፈጻሚ አካል እንዲኖር ማድረግ፣ በመንግሥት አሰራር ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር መዘርጋት፣ ነጻ የጸረሙስና ተቋም ማቋቋም፣ ጠንካራ የሲቪል ማህበረሰብ መፍጠር፣ በጸረሙስና ትግሉ ውጤታማ የሚያደርጉ ስልቶች እንደሆኑ ይጠቀሳሉ።

ሙስናን ለመከላከል የሚደረጉ ጥረቶች በመንግሥትና በተወሰኑ ተቋማት እንቅስቃሴ ብቻ የሚፈለገውን ያህል ውጤት ሊያመጡ እይችሉም። የፀረሙስና እንቅስቃሴዎች ውጤታማ እንዲሆኑ በሰፊ ህዝባዊ ተሳትፎና ድጋፍ ላይ መመሰረት ይኖርባቸዋል። ከዚህ አንጻር በርካታ አገራት ሙስናን ለመዋጋትና ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን ባላድርሻ አካላት በጸረሙስና ትግሉ ዙሪያ በማሰለፍና የጸረሙስና ጥምረት በመመስረት በቅንጅት እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ።